
# ያልወረዱ የወንዴ የዘር ፍሬዎች (UDT)

ያልወረደ የወንዴ የዘር ፍሬ (UDT) ማለት አንዱ ወይም ሁለቱም የወንዴ የዘር ፍሬዎች ወደ ዘር ከረጢት ከመውረድ ይልቅ በልጅዎ ሆድ አካባቢ (ሆድ) ውስጥ ሲቆዩ የሚፈጠር ሁኔታ ነው።

## ያልወረዱ የወንዴ የዘር ፍሬዎች ወይም UDT ምንድን ናቸው?

የወንዴ የዘር ፍሬዎች (ቴስተስ) 2 የዕንቁላል ቅርጽ ያላቸው የወንድ ብልት ይዘው በሚወለዱ ልጆች ላይ የሚገኙ ዕጢዎች ናቸው። መቀመጫቸውም ከብልት ዝቅ ብሎ በሚገኝ ከረጢት (የዘር ከረጢት) ውስጥ ነው። ስፐርም ማዘጋጀትና ሆርሞን ማመንጨት ይሰራሉ። አንድ ልጅ ከመወለዱ በፊት፣ የወንዴ የዘር ፍሬዎች ከኩላሊቶች አጠገብ በሰውነት ክፍል ውስጥ ያድጋሉ። በአብዛኛዎቹ ልጆች ላይ በመጨረሻዎቹ ጥቂት የእርግዝና ወቅቶች ላይ ወደ የዘር ፍሬ ከረጢት ተጉዘው ይገባሉ።

ያልወረዱ የወንዴ የዘር ፍሬዎች ሌላ መጠሪያቸው UDT ወይም cryptorchidism (kript-ORK-id-izm) ሲሆን ወደ የዘር ፍሬ ከረጢት አይገቡም። በቀላሉ ወደታች ወደ ከረጢቱ ሊገፉ አይችሉም።




ያልወረደ የወንዴ የዘር ፍሬ በሆድ አካባቢ ይቆያል

## ልጄ UDT እንዳለው እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ልጅዎ UDT እንዳለው ለማወቅ የተሻለው ዘዴ አካላዊ ምርመራ ማድረግ ነው። የወንዴ የዘር ፍሬ አልትራሳውንድ አስፈላጊ አይደለም።

የልጅዎ የወንዴ የዘር ፍሬ(ዎች) በከረጢታቸው ውስጥ ካልሆኑ፣ የዘር ፍሬውን ከሆድ አካባቢ (ሆድ) በእርጋታ ወደ ታች ለመግፋት እንሞክራለን። ይህን ለማድረግ፣ ሐኪሙ የጣታቸው ጫፍ ላይ ሎሽን ተቀብተው የዘር ፍሬዎቹ ከሚወርዱበት የልጅዎ ሆድ አካባቢ እጃቸውን ማንሸራተት ይችላሉ። ኩላሊት አካባቢ ጫና በማድረግ የዘር ፍሬውን ለማግኘት ወደ የዘር ፍሬ ከረጢት እጅን ማዞር (ሲዳሰስ የሚሰማ መሆኑን ማየት) ይችላሉ።

ልጅዎ ዘና ሲል እና በመጫወቻ ወይም ሌላ መሳሪያ ሃሳቡ ሲወሰድ የተሻለ ነው። አብዛኛውን ጊዜ፣ በዚህ ምርመራ ወቅት ልጅዎን ለመደገፍ Child Life Therapist (የሕጻናት ሕይወት ቴራፒስት) እንዲገኝ ማድረግ እንችላለን።



**ተጨማሪ ለማወቅ**

- ዩሮሎጂ
  206-987-2509
- የልጅዎን የህክምና አቅራቢ ይጠይቁ
- seattlechildrens.org

**ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎቶች**

- በሆስፒታል ውስጥ ከሆነ፣ ነርስዎን ይጠይቁ።
- ከሆስፒታል ዉጪ ለሆነ ቦታ፣ ነጻ የቤተሰብ የትርጉም መስመር ላይ በ 1-866-583-1527 ላይ ይደዉሉ። ለአስተርጓሚው የሚፈልጉትን ስም ወይም የውስጥ መስመር ይንገሩ።

Seattle Children's
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

## UDT የሚታከመው እንዴት ነው?

- የልጅዎ ዕድሜ 6 ዓመት እስከሚሞላው ድረስ የዘር ፍሬ(ዎች) ወደ ታች ካልመጡ (ካልወረዱ)፣ የቀዶ ጥገና እንዲደረግ እንመክራለን። የወንዴ የዘር ፍሬ(ዎችን) ወደ ዘር ከረጢት ለማውረድ የሚካሄድ ቀዶ ጥገና orchiopexy (or-kee-oh-PEK-see) ይባላል።
- በሕክምና ሒደቱ ወቅት፣ ለልጅዎ መድኃኒት (ሙሉ ማደንዘዣ) እንሰጣለን፣ ስለዚህ ሙሉ በሙሉ እንቅልፍ ላይ ይሆናል እንዲሁም ህመም አይሰማውም ማለት ነው። የወንዱ የዘር ፍሬ በሚገኝበት ቦታ ላይ በመመርኮዝ፣ 1 ወይም 2 ትናንሽ ስንጥቆች (መቆረጥ) በዘር ከረጢት፣ በብሽሽት ወይም በሆድ ላይ እንከፍታለን። ይህም የቀዶ ጥገና ሐኪሙ ወደ ዘር ፍሬው እንዲደርሱ እና ወደ ዘር ከረጢቱ እንዲያወርዱት ያስችላቸዋል።
- የተከፈተውን ቦታ ለመዝጋት የቀዶ ጥገና ሐኪሙ በጣም ቀጭን ስፌቶችን ይጠቀማሉ። ስፌቶቹ በቆዳ ውስጥ ይቀልጣሉ፣ ይሁን እንጂ ይህ ብዙ ሳምንታት ሊወስድ ይችላል። ስፌቶቹን ማውጣት አያስፈልገንም።

## የUDT ቀዶ ጥገና የሚመከረው ለምንድን ነው?

ሁልጊዜ በሆድ ውስጥ ወይም በብሽሽት አካባቢ የሚቆዩ የወንዴ የዘር ፍሬዎች ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ። በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ የቀዶ ጥገና ሕክምና እንዲደረግ እንመክራለን፡

- የወንዴ የዘር ፍሬዎች እነዲያድጉና የዘር ፈሳሽ እንዲዳብር የተሻለ ዕድል ይፈጥራል።
- የወንዴ የዘር ፍሬው የመቆልመ (የወንድ የዘር ፍሬ መዞር) እድሉ አነስተኛ ነው።
- የወረደ የወንዴ የዘር ፍሬ ልጅዎ በጉርምስና እና በአዋቂነት እድሜ ላይ ሲደርስ ወርሃዊ የወንዴ የዘር ፍሬ ምርመራዎች እንዲደረጉ ያስችላል።

## በቀዶ ጥገናው ዕለት ምን መጠበቅ አለብኝ?

ልጅዎ ቀዶ ጥገናው በሚደረግበት ቀን ከእርስዎ ጋር ወደ ቤት ይመለሳል። የቀዶ ጥገና ሐኪምዎ እና ነርሶች ከቀዶ ጥገናው በኋላ ቤት ውስጥ ልጅዎን እንዴት መንከባከብ እንዳለብዎት ይነግሩዎታል።

Seattle Children’s መስማት ለተሳናቸዉ፣ መስማት ለሚቸገሩ ወይም ከእንግሊዝኛ የተለየ ቋንቋ ለሚናገሩ ታካሚዎች፣ የቤተሰብ አባላትና የህግ ተወካዮች፣ ነፃ የአስተርጓሚ አገልግሎቶች ይሰጣል። በጥያቄ መሰረት የ Seattle Children’s ይህን መረጃ በአማራጭ ፎርማቶች እንዲገኝ ያደርጋል። ለቤተሰብ ሃብት ማዕከል በ 206-987-2201 ላይ ይደዉሉ። ይህ የመረጃ መስጫ ጽሁፍ በ Seattle Children’s ክሊኒካል ሰራተኞች ተገምግሟል። ነገር ግን፣ የእርስዎ ፍላጎቶች ልዩ ናቸዉ። ወደተግባር ከመግባትዎ ወይም በዚህ መረጃ ላይ ተመስርተው ከመወሰንዎ በፊት፣ የልጅዎን የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ያነጋግሩ።

2/24
PE984AM

© 2024 Seattle Children’s፣ Seattle፣ Washington። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነዉ።


# Undescended Testicles (UDT)

An undescended testicle (UDT) is when 1 or both testicles stay inside of your child's belly area (abdomen) instead of moving down into the scrotum.

## What are undescended testicles or UDT?

Testicles (or testes) are 2 oval shaped glands in babies born with a penis. They sit in the sac of skin below the penis (the scrotum). They make sperm and produce hormones. Before a baby is born, the testicles grow inside the body, near the kidneys. During the last few months of pregnancy, in most babies, they travel down into the scrotum.

Undescended testicles, also called UDT or cryptorchidism (kript-ORK-id-izm), do not move into the scrotum. They cannot be gently pushed down into the sac.




**An undescended testicle stays in the belly area**

## How do I know if my child has an UDT?

The best way to know if your child has an UDT is by doing a physical exam. A testicle ultrasound is not necessary.

If your child's testicle(s) are not in their scrotum, we will try to gently push the testicle down from the belly area (abdomen). To do this, the provider may put lotion on their fingertips and then slide their hand along the area of your child's belly from where the testicles descended. They will start putting firm pressure near the kidney and move down to the scrotum to feel for the testicle (see if it's palpable).

It is best if your child is relaxed and perhaps distracted with a toy or device. Many times, we can arrange to have a Child Life Therapist to help support your child with this exam.



### To Learn More

- Urology
  206-987-2509
- Ask your child's healthcare provider
- seattlechildrens.org

### Free Interpreter Services

- In the hospital, ask your nurse.
- From outside the hospital, call the toll-free Family Interpreting Line, 1-866-583-1527. Tell the interpreter the name or extension you need.

Seattle Children's®
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

## How is the UDT treated?

- If your child's testicle has not moved down (descended) by age 6 months, we recommend surgery. The surgery to bring down the testicle(s) into your child's scrotum is called orchiopexy (or-kee-oh-PEK-see).
- During the procedure, we will you give your child medicine (general anesthesia), so they will be fully asleep and not feel pain. Depending on the location of the testicle, we make 1 or 2 small cuts (incisions) in the scrotum, the groin or the abdomen. This allows the surgeon to reach the testicle and move it to the scrotum.
- To close the incision, the surgeon will use very fine stitches. The stitches dissolve in the skin, but it may take several weeks. We don't need to remove them.

## Why is surgery recommended for UDT?

Testicles that always stay inside the abdomen or groin area can develop problems. We recommend surgery for the following reasons:

- It gives the testicles the best chance for growth and sperm development.
- The testicle is less likely to twist (have testicle torsion).
- The descended testicle will allow for monthly testicle exams when your child is an adolescent and an adult.

## What should I expect the day of surgery?

Your child will go home with you on the same day as the surgery. Your surgeon and nurses will tell you how to care for your child at home after their surgery.

Seattle Children's offers free interpreter services for patients, family members and legal representatives who are deaf or hard of hearing or speak a language other than English. Seattle Children's will make this information available in alternate formats upon request. Call the Family Resource Center at 206-987-2201. This handout has been reviewed by clinical staff at Seattle Children's. However, your needs are unique. Before you act or rely upon this information, please talk with your healthcare provider.

© 2024 Seattle Children's, Seattle, Washington. All rights reserved.

2/24
PE984